መልእክት ዘጠኝ

## የእስራኤል ልጆች ንጉሥ የሌላቸው መሆናቸው
## እና ሰው ሁሉ በፊቱ ትክክል መስሎ የታየውን ማድረጉ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡ መሣ. 2፡10-18፤ 3፡7-15፤ 8፡33-35፤ 10፡6-7፤ 13፡1፤ 17፡5-6፤ 18፡1፣ 30-31፤ 19፡1፤ 21፡25

**I. በዝቅጠቱ እስራኤል በአገዛዝ፣ በአምልኮ እና በስነ-ምግባር የተቃወሰ ሆነ—መሣ. 3፡7-15፤ 8፡33-35፤ 13፡1፤ 17፡5-6፤ 18፡30-31፡-**

ሀ. የእስራኤል ልጆች እንደርስታቸው ምድሩን የራሳቸው ካደረጉ በኋላ፣ በከነዓን የሚኖሩትን ሰባቱን ነገዶች ፈፅሞ ለማስወጣት እና ለማጥፋት የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አልታዘዙም—1፡27-36።

ለ. በውጤቱም፣ የእስራኤል ልጆች አማልክቶቻቸውን አገለገሉ፣ በዚህም በጌታ ፊት ክፉ አደረጉ—2፡10-18።

ሐ. የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ያወጣቸውን የአባቶቻቸውን ጌታ አምላክ ተዉ፣ በዙሪያቸውም የነበሩትን ሰዎች አማልክት ተከተሉ፤ ለእነርሱም ሰገዱላቸው፣ ያሕዌንም አስቆጡት—10፡6-7።

መ. እግዚአብሔርም ወደ ማራኪዎች እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፣ ከዚያ ወዲያ መቋቋም እንዳይችሉ በጠላቶቻቸውም እጅ አሳልፎ ሰጣቸው፤ በወጡበት ጊዜ ሁሉ፣ የጌታ እጅ ትከፋባቸው ነበረች—2፡11-15።

ሠ. በእስራኤላውያን ታሪክ የመሣፍንት ዘመን የጨለማው ጊዜ ተብሎ ሊቆጠር ይችላል፤ አሳዛኝ ጊዜም ጭምር ነበረ።

ረ. በዚያን ጊዜ፣ በእስራኤል ልጆች መካከል በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ፣ ጣዖት አምልኮ (ምዕ. 17—18)፣ ግጭት (ምዕ. 9)፣ በነገዶቹ መካከል ጠላትነት እና ውዝግብ (ምዕ. 20—21)፣ ዝሙት (ምዕ. 19)፣ ርኩሰት፣ የጭካኔ ግድያዎች እና ሁሉም ዓይነት የከፋት ሥራ ነበሩ።

**II. "በዚያን ዘመን በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም፤ እያንዳንዱም ሰው መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር"—21፡25፡-**

ሀ. የእስራኤል ሕዝብ በመካከላቸው ንጉሥ አልነበረም ሲሉ፣ ይህ ማለት እግዚአብሔርን እና ሕጉን ሽረዋል እንዲሁም ለእግዚአብሔር ንግሥና ዕውቅና አልሰጡም ማለት ነው—17፡6፤ 18፡1፤ 19፡1።

ለ. የእግዚአብሔር ማደሪያው ድንኳን በሴሎ የነበረ እና ሊቀ ካህናቱ ኡሪም እና ቱሚም የነበረውም ቢሆንም እንኳን፣ እስራኤል ንጉሣቸው የሆነውን እግዚአብሔርን እና ሕጉን ስለሻሩ በእስራኤል አገዛዝ፣ አስተዳደር አልነበረም፣ በመሆኑም በመጽሐፈ መሣፍንት ውስጥ የእግዚአብሔር መገለጥ አልነበረም—18፡31፤ ዘጸ. 28፡30፣ የግርጌ ማስታወሻ 1።

ሐ. መሣፍንት በነበሩበት ጊዜ በእስራኤል ንጉሥ ስላልነበረ፣ የእስራኤል ልጆች በፊታቸው ትክክል መስሎ የታያቸውን አደረጉ፣ ከዚያም የተነሣ የበሰበሱና የተበላሹ ሆኑ—መሣ. 17፡6፤ 18፡1፤ 19፡1፤ 21፡25፡-

1. ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ መልካሚቱ ምድር ሲገቡ በፊታቸው ትክክል መስሎ የታያቸውን በእግዚአብሔር ፊት ግን ትክክል ያልሆነውን እንዳያደርጉ ነገራቸው—ዘዳ. 12፡8-14።
2. ሰይጣን የእስራኤል ሕዝብ በፊታቸው ትክክል መስሎ የታያቸውን እንዲያደርጉ፣ አመጸኛና እና አምላክ-የለሽ፣ የእግዚአብሔርንም መገደብ የሚጥሉ እንዲሆኑ አደረጋቸው፤ ይህ በመሣፍንት 17—18፤ 19፡1፤ እና 21፡25 ተገልጧል።
3. ዛሬ አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች የሆነን ነገር ለእነርሱ ትክክል ወይም ስህተት ነው ይላሉ፤ በዚህ መንገድ መኖር በፊታችን ትክክል መስሎ የታየንን ማድረግ ነው።
4. ለእኛ በፊታችን ትክክል መስሎ የታየንን ማድረግ በጣም አስፈሪ ነው፤ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ማድረግ አለብን—ዘዳ. 12፡8።

መ. በእስራኤል ንጉሥ ባልነበረ ጊዜ፣ ሥልጣን አልነበረም፣ ሕዝቡም ደስ ያሰኛቸውን ያደርጉ ነበር፤ ይህ ልክ በአሁኑ ክፉ ዘመን፣ በዓለም እና ኃይማኖታዊ ሥርዓት በሆነው ክርስትና ውስጥ ያለ የነገሮች ሁኔታ ነው—ኤፌ. 2፡2፣ 12።

ሠ. በጌታ ምለሳ ውስጥ በመሣፍንት ውስጥ ከተገለጠው ዓመጽ ነፃ መውጣት እና በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር መኖር የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ማድረግ ያስፈልገናል—ቲቶ 2፡14፤ ገላ. 1፡4፤ ማቴ. 6፡10።

**III. እግዚአብሔር የዘመናት ንጉሥ፣ ፈጽሞ የማይለዋወጥ ለዘላለም ፍጹም ስልጣን ያለው ነው—1 ጢሞ. 1፡17፡-**

ሀ. የምናምንበት፣ የምናገለግለው እና ወደ ውስጣችን እየታደለ ያለው አምላክ የዘመናት ንጉሥ፣ የዘላለም ንጉሥ ነው—ቁ. 17፤ 2 ቆሮ. 13፡14።

ለ. ክርስቶስ የተወለደው የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት የሚንከባከብ ንጉሥ፣ ገዢ ለመሆን ነው፣ እርሱ አሁን የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ ነው—ማቴ. 2፡2፣ 6፤ ራዕ. 19፡16፤ 17፡14፡-

1. እንደ ንጉሥ፣ ክርስቶስ ያሕዌ እግዚአብሔር ነው፣ እንዲሁም ደግሞ ሰው ነው—መዝ. 24፡8፣ 10።
2. ክርስቶስ በልባችን ውስጥ እየገዛ ያለው ንጉሣችን እንደሆነ መገንዘብ እና በንግሥናው ሥር በምንኖርባቸው አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለክርስቶስ ንግሥና እውቅና መስጠት አለብን—ኤፌ. 3፡17፤ 1 ጢሞ. 3፡15፤ 6፡15።
3. ክርስቶስ እንደ የክብር ንጉሥ—እንደ የሠራዊት አለቃ፣ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት ውስጥ በሚነግሠው ድል-በነሣው እና በሚመጣው ክርስቶስ ውስጥ አካል እንደለበሰው እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ—ይመጣል—መዝ. 24፡7-10።
4. ክርስቶስ በመንግሥቱ በዳዊት ዙፋን ላይ መግዛቱ በመጀመሪያ በሺው ዓመት መንግሥት በመቀጠልም ለዘላለም በአዲሱ ሰማይ እና በአዲሱ ምድር ይሆናል—ኢሳ. 9፡7፤ ሉቃ. 1፡33፣ የግርጌ ማስታወሻ 1።
5. "ዙፋን በፍቅር ይመሠረታል፤ ከዳዊት ቤት የሆነ፣… አንድ ሰው በታማኝነት በላዩ ይቀመጣል"—ኢሳ. 16፡5 (አ.መ.ት.)፡-

   ሀ. ክርስቶስ በዳዊት ድንኳን መግዛቱ መጽናናትን፣ መበረታታትን እና መታደስን ያመለክታል።

   ለ. የክርስቶስ ዙፋን በአፍቃሪ ቸርነት እና በርኅራኄ ይመሠረታል፣ በዙፋኑም ላይ በእውነት፣ ማለትም፣ በእውነተኛነት እና በታማኝነት ይቀመጣል—ቁ. 5።

   ሐ. መንግሥቱን ከአፍቃሪ ቸርነት፣ ከእውነተኛነት፣ ከታማኝነት፣ ከፍትህ እና ከጽድቅ ጋር በማምጣት ክርስቶስ በውስጣችን እንዲገዛ ከፈቀድንለት፣ በእነዚህ ሰናይ ባሕርያት ከእርሱ ጋር አንድ አይነት እንሆናለን—ቁ. 5።

**IV. ከዓመጽ እና የዓመጽ ሠራተኞች ከመሆን መዳን እና እግዚአብሔርን የማገልገልን መርህ በመታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ነገር ማድረግ ያስፈልገናል—ቲቶ 2፡14፤ ማቴ. 7፡21-23፡-**

ሀ. በፊታችን ትክክል መስሎ የታየንን ማድረግ ዓመፅ ነው—መሣ. 21፡25፡

1. "ኃጢአትም ዓመፅ ነው"፤ በመሆኑም፣ ዓመፅ ኃጢአት ነው፣ ወይም፣ በተገላቢጦሽ፣ ኃጢአት ዓመፅ ነው—1 ዮሐ. 3፡4፡-

   ሀ. በ 1ኛ ዮሐንስ 3፡4 "ዓመፅ፣" ወይም ያለ ሕግ መሆን፣ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሰው ላይ ካለው የመግዛት መርህ ውጪ መሆን ወይም እግዚአብሔር በሰው ላይ ካለው የመግዛት መርህ ሥር አለመሆን ነው።

   ለ. ኃጢአትን ማድረግ ያለ ሕግ መሆን፣ ሕግን መተላለፍ ነው።

   ሐ. በእግዚአብሔር ዓይኖች፣ ሰው ኃጢአትን የሚያደርገው በእኔነት-ፈቃድ በመመላለስ እና በእግዚአብሔር ሥልጣን ላይ በማመፅ በራሱ ተፈጥሮ እና ፈቃድ መሠረት ሲያደርግ ነው።

   መ. ዓመፅ ለእግዚአብሔር ሥልጣን እውቅና አለመስጠት እና አለመገዛት ነው።

   ሠ. ዓመፅን በተግባር መለማመድ እግዚአብሔር በሰው ላይ ካለው የመግዛት መርህ ውጪ የሆነ ሕይወት መኖር እና እግዚአብሔር በሰው ላይ ካለው የመግዛት መርህ ሥር አለመሆን ነው፤ የአሁኑ ዘመን በሕግ-አልባነት እና በዓመፅ የተሞላ ነው።

   ረ. በዓመፅ ውስጥ አንድ ሰው በሥልጣን ላይ ማመፅ ብቻ ሳይሆን ሕግ እንደሌለ ያህል ይንቀሳቀሳል።

2. ክርስቶስ ገንዘቡ የሚሆነውን የተለየ ሕዝብ ለራሱ ለማንፃት፣ ከዓመፃ ሁሉ ሊቤዠን ስለ እኛ ራሱን ሰጥቷል—ቲቶ 2፡14።

ለ. "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም"—ማቴ. 7፡21፡-

1. ጌታን መጥራት ለመዳናችን ይበቃናል፣ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ግን፣ የሰማዩ አባታችንን ፈቃድ ማድረግ ያስፈልገናል—ሮሜ 10፡13፤ 12፡2፤ ማቴ. 12፡50፤ ኤፌ. 5፡17፤ ቆላ. 1፡9።
2. ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት የሰማዩ አባታችንን ፈቃድ ማድረግ ስለሚጠይቅ፣ በዳግም ውልደት በኩል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከመግባት ጋር በግልፅ የተለየ ነው—ዮሐ. 3፡3፣ 5፡-

ሀ. ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መግባት የሚገኘው ከመለኮታዊው ሕይወት በመወለድ ነው—1፥12-13፤ 3፥5-6።

ለ. ወደ መንግሥተ ሰማያት ውስጥ መግባት የሚገኘው መለኮታዊውን ሕይወት በመኖር በኩል ነው—ማቴ. 7፥21፤ 12፥50።

ሐ. ጌታ ኢየሱስ በስሙ የተነበዩትን፣ አጋንንት ያወጡትን፣ እና የኃይል ሥራዎችን የሠሩትን የገሰጸበት ምክንያት፣ እንደ ዓመፅ ሠራተኞች፣ እነዚህን ነገሮች ያደረጉት ከራሳቸው እንጂ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመታዘዝ የወጣ ስላልሆነ ነው—7፥23፦

1. በአጽናፍ-ዓለም ሁለት መርሆች አሉ—የእግዚአብሔር ሥልጣን መርህ እና የሰይጣን ዓመፅ መርህ—ሐዋ. 1፥7፤ ኢሳ. 14፥13-14፦

   ሀ. በአንድ በኩል እግዚአብሔርን ማገልገል በሌላ በኩል የዓመፅን መንገድ መውሰድ አንችልም፤ ከሕግ-አልባነት መርህ መዞር እና የዓመፅን መንገድ መተው አለብን—ማቴ. 28፥18፤ ይሁ. 11።

   ለ. እግዚአብሔርን ማገልገል በቀጥታ ከሥልጣኑ ጋር የተገናኘ ነው፤ የሥልጣንን ጉዳይ ካልፈታነው፣ በአገልግሎታችን ዘርፎች ሁሉ ችግሮች ይኖሩናል።

2. ጌታ ለእግዚአብሔር ሥልጣን እና ለአብ ፈቃድ በመገዛት መርህ ውስጥ አገልግሎታችንን ይጠብቀው—ሐዋ. 1፥7፤ ማቴ. 7፥21፤ 12፥50።

## V. በመጽሐፈ መሣፍንት ውስጥ የተዘገበው በአገዛዝ፣ በአምልኮ፣ እና በስነ ምግባር ያለው ቀውስ በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ ያለውን ሰይጣናዊ ቀውስ በስእል ያሳያል—ዘፍ. 3፥1-5፤ ራእ. 20፥10—21፥4፦

ሀ. አጽናፍ-ዓለም በቀውስ ሁኔታ ውስጥ ነው፤ ይህ ቀውስ በዛሬው ዓለም ውስጥ ያለው የመከራ ምንጭ ነው፣ በፍጥረት ውስጥ ቀውስ እስካለ ድረስ፣ በዓለም ውስጥ መከራዎች ይኖራሉ—ሮሜ 8፥18-22።

ለ. የአጽናፍ-ዓለም ታሪክ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ታሪክ እና የሰይጣን ቀውስ ነው—ዘፍ. 1፥1-2፣ 26፤ ራእ. 20፥10—21፥4፦

1. ሰይጣን፣ ዲያቢሎስ፣ ክፉ የሆነው ቀውስ ምንጭ እና ንጥረ-ነገር ነው—ማቴ. 16፥23፤ ራእ. 2፥9-10፤ 2 ቆሮ. 2፥11፤ 1 ጴጥ. 5፥8።

2. እግዚአብሔር ራሱ መለኮታዊው ኢኮኖሚ ነው፣ ሁሉንም ነገር በሥርዓት ለማስቀመጥ እንደ አስተዳደር፣ አዘገጃጀት እና እቅድ ወደ እኛ ውስጥ መጥቷል—ኤፌ. 1፥10፤ 3፥10።

3. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እና በልምምዳችን፣ ሰይጣናዊው ቀውስ ሁልጊዜ ከመለኮታዊው ኢኮኖሚ ጋር አብሮ ይሄዳል፣ የእግዚአብሔርንም ኢኮኖሚ በእርግጥ ይረዳል—ቁ. 9።

ሐ. በቀውስ፣ በዓመፅ እና በሕግ-አልባነት መካከል እንደሚኖሩ ሰዎች፣ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ግልጽ ራእይ ሊኖረን ይገባል—መዝ. 2፥1-6፤ ምሳ. 29፥18፤ ኤፌ. 3፥9፦

1. በዚህ ራእይ መገዛት፣ ቁጥጥር ሥር መሆን እና መመራት ያስፈልገናል—ሐዋ. 26፥19።

2. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ፣ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድ ራእይ ጠንካራ እና የማንናወጥ መሆን አለብን—ኤፌ. 1፥10፤ 3፥9፤ ራእ. 4፥11፤ 1 ቆሮ. 15፥58፤ ዕብ. 12፥28።

መ. ድል-ነሺዎቹ በአሮጌው ፍጥረት ውስጥ ያለውን ሰይጣናዊው ቀውስ ያሸንፋሉ፣ ለአዲሱ ፍጥረትም መለኮታዊውን ኢኮኖሚ ይፈጽማሉ—1 ጢሞ. 1፥4፤ ኤፌ. 1፥10፤ 3፥9-10፤ 2 ቆሮ. 5፥17፤ ገላ. 6፥15፦

1. ድል ነሺዎቹ ከሰይጣናዊው ቀውስ አርነት አልወጡም፤ በምትኩ፣ አጥፊ የሆነውን ሰይጣናዊ ቀውስ ያሸንፋሉ፣ በሚገነባው መለኮታዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ድል ያደርጋሉ—1 ጢሞ. 1፥3-4፣ 19-20፤ 4፥1-2፤ ቲቶ 3፥10፤ 2 ጢሞ. 1፥15፤ 4፥8።

2. ድል ነሺዎቹ በቀውሱ ሲሰቃዩ፣ "..በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ" (2፥1) ይበረታሉ፣ ለመለኮታዊው ኢኮኖሚ መቆም እና መኖርም ይችላሉ—1፥10-15፤ 3፥14-17፤ 4፥2፣ 5፣ 7፣ 18።

© 2021 Living Stream Ministry